ርብርቡ ወደ መስረታዊው መፍትሄ ማቅናት አለበት

የህዝቡን ፍላጎትና መብት የሚረግጥ፥ የሃገር ጥቅምና ሉአላዊነት የማይጠብቅ መንግስትተብየው አህአዲግ በስ ልጣን ላይ እስካለ ድረስ ኤትዮጵያ ወደፊት የመራመድ እድልዋ ይሁን ህዝቡ በውል የመበልጸግ ምኞቱ የማ ይጨበጡ ህልሞች ሆነው ይቆያሉ። የህዝቡ መብትና የሃገሪቱ ጥቅም ለማስከበር ምን አይነት መሰረተሰፊ ስ ርአት መፍጠር እንዳለብን፥ በተለይ አሁን ከምንገኝበት አሳዛኝ ደረጃ ተነስተን ስናሰናስላው እጅግ ከባድና ውስብስብ ትግል የሚጠይቅ ለመሆኑ መገንዘብ የግድ ይላል። ይህን ባለመገንዘብ እና ወሳኙ አቅጣጫ ሳይጨ በጥ የሚደረገው ትግል ትርፉ ድካም ለመሆኑ ያለፈው የአስር አመታት ልፋት እንደ አስረጅ ማቅረብ በቂ ይመስለናል።

እንዲያው መፍትሃ ላይገኝ፣ በየወቅቱ ገንፍለው በሚነሱ ሃገራዊ ጉዳዮች ዙርያ ላይ በመነሳሳት የኢትዮጵያ ህዝ ቦች፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ እንዲሁም የሙያና ሲቪክ ማህበራት ብዙ ታግለዋል፤ አያሌ መስዋእትነት ከፍለዋ ል። አስራአንድ አመታት ሙሉ ያለመታከት በትግል ይጠመዱ እንጂ ለዛ ሃገራዊ ጥያቄና ህዝባዊ ፍላጎት የ ሚያንጸባርቅ መፍትሃ ገና ጠብም አላለም። ሁሉም በየፊናው እየታገለ ነው፥ በግለሰብ ደረጃም ይሁን ትግሉ ቀጥለዋል፥ መፍትሃው ግን አሁንም ብቅ ሲል አይታይም፥ ምክንያቱስ ምንድን ነው ብሎ መጠየቅና መፍትሄ ውንም መሻት ርዕሰ ጉዳይ አድርገን አቅርበነዋል። በርግጥ ችግሮቹ ብዙ ናቸው፤ ይሁን እንጂ ወቅቱ ባነሳው ከፊል ጥያቄአችን፥ ማለትም የባህር በር መብትና የድንበር መካለል ጉዳይ ጋር አስታክከን አንዱ መሰረታዊ ችግር እንቃኛለን።

አንዱ ትልቁ ችግራችን የተናጠል መፍትሃ በመሻት የሚደረግ ርብርቦሽ ነው። ይህም ማለት ዘላቂ መፍትሃ በ ሚያመጣው ቁልፍ ጥያቄ ላይ እንደመረባረብ ፈንታ በቁልፉ ጥያቄ ዙርያ በተንጠለጠሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላ ይ ወቅታዊ ርብርቦሽ በማድረግ መጠመድ ነው። እሩቅ ሳንሃድ ባለፈው የምርጫ ጋጋታ፥ ምርጫው ፍትሃዊ ለውጥ ያመጣ ይመስል፤ በኤትዮኦርትራ ጦርነት፥ ጦርነቱ መሰረታዊ መፍትሃ ያስከትል ይመስል፤ በህወሓትኤ ህአዴግ አመራር መፍረስ፥ ከፍርስራሹ አዲስ ስርአት ይታነጽ ይመስል፤ ብዙ ህዝባዊ፥ ድርጅታዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ሲግሉና ሲበርዱ፤ ሲደክሙና ሲያርፉ ታይተዋል። የመሰረታዊው መፍትሃ አቅጣጫ ግን ሊጨበ ጥ ይቅርና እይታ ውስጥ ሊገባም አልበቃም። አሁን ተራው የደረሳቸው ወቅታዊ ጥያቄዎች፥ የድንበር መካለ ል ክርክርና የባህር በር ጉዳይ መድረኩን ይዘውታል። በሌላ ወቅታዊ ጥያቄ እስኪገፉ ድረስም አንቀሳቃሽ አ ጀንዳዎች ሆነው ይሰነብታሉ። እንደተለመደው።

በርግጥ ከፍትሃዊ ምርጫ ጀምሮ እስከ የባህር በር ጉዳይ ድረስ፣ በተለይም የድንበር መካለልን፥ የሰብአዊ መ ብቶች መከበርን፥ የክልል ፖለቲካን ጨምሮ እልባት ያላገኙ አያሌ ህዝባዊና ሃገራዊ ጥያቄዎች በውዝፍ አሉ ን። እነዚህ ጥያቄዎች ለተቀናጀ ትግል የሚጋብዙ አበይትና አንገብጋቢ ጉዳዮች ለመሆናቸው አላማውከንቱ አ ህአዴግ በስተቀር የሚጠራጠር ሰው ያለ አይምስለንም። በዚህ ላይ አምባገነኖቹ አህአዴጎች በስልጣን ላይ እስ ካሉ ድረስ እነዚህ የተጠቀሱት አበይት ጉዳዮች ይሁን ሌሎች ሃገራዊ ጥያቄዎች በተናጠልም ይሁን በጋራ መ ፍትሔ ያገኛሉ ማለት ደግሞ ዘበት ነው። እነሱ እንደሆነ ድሮም ይሁን አሁን ከልብ የመነጨና የሚዋደቁለ ት ሃገራዊ ራዕይም አጀንዳም የላቸውም። የብሔር አጀንዳስ ቢሆን፥ ጠለቅ ብሎ ከታየ ለጽንፈኞቹ የወሬ ቅ ንብር የሚበጅ ካልሆነ በስተቀር ከየት መጥቶ። አንዳንድ የመንደር ፖለቲከኞች እንደሚያናፍሱት የአውራጃዊ አጀንዳም ሊኖራቸው አይችልም። በቅጡ ከታየ እኮ አውራጃ፥ ወረዳ ወይም ቀበሌ ውስጥ ለሚገኝ ምዝብር ህዝብ መብትና ጥቅም መከበር እምነቱ ከኖረ በብሃር ወይም በሃገር ደረጃ ለታቀፈው ህዝብ መብትና ጥ ቅም መቆም እስከዚህ አይከብድም ነበር። ህዝባዊ ነገር ሁሉ ለአህአዴግ ምኑም አይደለም። የነዚህ ሰዎች አጀ ንዳ፥ የተፈለገው ቀለም ቢቀቡትም ባይቀቡትም ስልጣን እንደምንም ጨብጦ ይዞ የግል ሃብትን ማግበስበስ መሆኑ ምርምር የማይጠይቅ እውነታ ነው። ዝርዝር ውስጥ መግባትም አያስፈልግም። ይህ እውነታ እሩቅ ሳን ሃድ ካጥለቀለቃቸው ሙስናና ካመነመናቸው የርስበርስ መበላላት ደቋ መረዳት ይቻላል።

ሃገራዊ አጀንዳንና ህዝባዊ አቂዋምን በስልጣንና በሙስና የተኩ ሰዎች ሃገራዊና ህዝባዊ ጉዳዮች ሊያስፈጽሙ አይጠበቅባቸውም። አለዚያ <u>ሳም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ መሄድ</u> ሊሆን ነው። ለስልጣናቸውና ለግል ሃብት ሲሉ ሃገሩም በታትነው ቢሸጡ፥ ህዝቡንም አተራምሰው ቢያፍኑ ደንታ የላቸውም። አስራአንድ አመታት ሙሉ የተገነዘብንላቸው ፍጻሜ ካለ ይህ እውነታ ነው። ችግሩ ይህ ብቻም አደለም። እነዚህ ሰዎች ሃገራዊ ጥቅምና ህዝባዊ መብት ለማስከበር የሚደረገውን ትግል ለማኮላሸት የተዘጋጁም ናቸው።

እንግዲህ ይህ አይነት መንግስት ስልጣን ላይ ተቀምጦ ሃገርንና ህዝብን በጉልበቱ ወክሎ፥ ውክልናው በአለም አቀፍ መድረኮች በተለይ ደግሞ በተባበሩት መንግስታት እውቅና አግኝቶ፥ በሃገሪቱና በህዝቡ መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ተደራዳሪ፥ ወሳኝም አስወሳኝም ሆነዋል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅትም አባል መንግስታቱ በነደፉት መዋቅር የሚተዳደር ማህበር በመሆኑ አትዮጵያን በተመለከተ አህአዴግ ብቻ ያቀረበለትን ጉዳይ መቀበል እንጂ በህዝቡ ወገን በኩል የሚቀርበው አቤቱታን የማስተናገድ ግዴታም ሃላፊነትም የለበት ም። አህአዴግ ይህነኑን አሰራር ጠንቅቆ ያውቃል፥ ለሰንካላው አላማውም ይጠቀምበታል። ስለዚህም የህዝቡ ፥ የተቃዋሚ ድርጅቶች፥ የሲቪክና የሙያ ማህበራት አቤቱታ በመንግስታቱ ድርጅት መድርክ ጩኸት ሆኖ የሚቀር እንጂ ሰሚ ጆሮ አግኝቶ ፍትሃዊ ውሳኔ የሚጎናጸፍ ጉዳይ አልሆነም፥ አይሆንምም።

በርግጥ በባህር በር፥ በድንበር መካለል፥ በፍትሃዊ ምርጫ ወዘተ በመሳሰሉ አበይት ጉዳዮች ላይ መረባረቡና አቤቱታ ማስተጋባቱ የተወሰኑ ጥቅሞች ይኖሩታል። ሁለት እንኳን ብንጠቅስ፥

1ኛ በያንዳንዱ ርዕሰ ጉዳይ ዙርያ በሳል ግንዛቤ እንድናገኝ አበክረን እንድንታገል ይረዳል ።

2ኛ ውሳኔ ሰጪዎቹ ፍርዳቸው ነገ መዘዘ ሲያስከተል ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ታሪካዊ ሰነድ ይሆናል ።

ከዚህ አልፎ የሚያመጣው ጥቅም አይታየንም ። ለነዚህ ከፊል ጉዳዮች በተናጠል መታገሉ ጉዳት ባይኖረውም መሰረታዊ መፍትሄ እንደሚያመጣ አድርጎ መቁጠር ስህተት ነው። የተጠቀሱት ሁለት ጥቅሞችም የርብርቦሹ ውጤቶች እንጂ የችግሮቹ መፍትሄ አይደሉም። ሊሆኑም አይችሉም። እንግዲህ የተናጠል ርብርቦሹ እዚህ አ ድርሶናል፤ ከዛም አያልፍም። ጥያቄው ግን ከዛ በላይ ነው።

በመሰረቱ የኢያሌ ችግሮቻችን መፍትሔ የሚገኘው እነዛ ሃገራዊና ህዝባዊ ችግሮች የራሴም ችግሮች ናቸው ብ ሎ በማመን ለመፍትሔአቸው በማንኛውም መድረክ የሚዋደቅ ህዝቡ ያቆመው መንግስት ሲኖር ብቻ ነው። ይህ ለሃገር ጥቅም የሚቆም ከህዝቡ በፈለቀው ህገ መንግስት የሚመራ አስተዳደር ሊኖር የሚችለው ለዚሁ ስ ርአት ጸር የሆነውን አምባገነኑን አህአዴግ ማስወገድ ቅድመ ሁኔታ ይሆናል። ሌላ አማራጭ መፍትሔ የለም። ስለዚህም ርብርቦሹ ኤህአዴግን አስወግዶ፥ በሌላ አምባገነን ቡድን እንዳይተካ ዘብ ቆሞ፥ ለሓቀኛ ሃገራዊ ጥቅም፥ ለህዝቦቹ መብት መከበር፥ እኩልነትና አንድነት የተሰለፈ፥ በሕገ መንግስት የሚገዛ አስተዳደር ለመ መስረት መሆን ይኖርበታል። ይህ አላማ ማእከል ያደረግ የትግል አቅጣጫ ካልተያዘ የትም መድረስ አይቻል ም።

በሃገሪቱ ውስጥና በውጭ እተቀጣጠለ ያለውን ተቃውሞ ከፊል ጉዳዮች ብቻ አንግቦ በመንቀሳቀስ ግቡ ሊመ ታ እንደማይችል በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል። እንቅስቃሴው ከዋናው ስትራተጂ ማለትም ኤህአዴግን ከማስ ወገድና በምትኩ ሃገራዊና ህዝባዊ ሃይል ከመመስረቱ ጋር መቀናጀት የግድ ይላል። ይህ ካልሆነ ግን እስካሁን በመጣንበት መንገድ መቀጠል ሊሆን ነው። እሱም ውጤት ላይኖረው እንዲያው መታገል፥ መጋል መቀዝቀዝ ፥ እንድያው መድከም ብሎም ከንፈር እየመጠጡ መኖር፥ መኖር ከተባለ መሆኑ ነውና።

እንግዲህ በየዘርፉ ያለው ትግል ፍርያማ እንዲሆንና ዘላቂ ውጤት እንዲያስገኝ ከተፈለገ አላማችን ምን እንደ ሆነና ወደ አላማችን እንዴት መድረስ እንደምንችል በግልጽ ውይይት ነድፈን የአቅማችን አስተዋጽኦ ማከል ይጠበቅብናል። ሃገር ወዳድነትና ህዝብ አፍቃሪነት ለህብረት ትግሉና ለጋራው አላማ መስዋእት በመክፈል እን ጂ ሓንድ ጽንፍ ይዞ በማቅራራት አይመዘንም። ባለፈው የትግል ጉዞአችን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የደቀን ናቸው እንቅፋቶችም ማስወገድ ይኖርብናል። ተቀራርቦ በግልጽ መድረክ መወያየት እያለ በርቀት መጎሻሸም፥ ሁሉም ኤትዮጵያዊ በእኩልነት እንዲራመድ መቀስቀስ ትቶ ከኔ በላይ አትዮጵያዊ ላሳር የሚለው ውዳሴ ከንቱ ቀረርቶ እያስተጋቡ ህዝቡን መከፋፈል ፣ ያው የኤህአዴግ ግልባጭ መሆን፥ ለሁሉም እኩል አይቶ የሚበይን ስርአት እስኪመሰረት እንደመታገል ፈንታ የትም ላይደረስ ደጋግሞ መካሰስና መወነጃጀል፥ በተቃዋሚ ድርጅ ት መሪ አካልና በምዝብር ህዝቡ መካከል ያለው መሰረት ሰፊ ገደል አስመስሎ በማቅረብ አጋር ታጋይን ማስከፋት፥ ከሚንጸባረቁ እንቅፋቶች አንዳንዶቹ ናቸው። እነዚህ እንቅፋቶች ከአምባገነኖቹ ክፉ ስልቶች ባላነሰ ለህዝቡ ትግል ደንቃራ ጋሬጣዎች ሲሆኑ ለገዢዎቹ ግን ተዝናንተው የሚራመዱበት ምንጣፍ ሆነው አገልግለ ዋል። የነዚህና መሳይ ደካማ አመለካከቶች ኣሉታዊ ተራ በሚገባ ተገንዝበን፥ በግልጽም እየተዋጋናቸው፥ ከቻ ልን የኣቂም ውህደት ፈጥረን፥ ይህ ካልተቻለም በጋራ ጉዳዮች ላይ ህብረት መስርተን አገር የሚያጠፉትን ማስወገድ ተቀዳሚ ተግባር ማድረግ አለብን።

ወሳኙ የትግል አቅጣጫ ማእከል ኣድርገን ከተጠቀሱት ኣመኬላዎች የጸዳ ጉዞ ከተከተልን በርግጥ ብዙ አመታ ት ሳናስቆጥር እግባችን ለመድረስ የሚያቆመን ሃይል አይኖርም። እላይ ከጠቀስናቸው እንቅፋቶች ባሻገር ሌላ እንቅፋት አይኖርም ማለት አይደለም። ባንድ በኩል በአምባገነኑ ስርኣትና በህዝቡ መካከል ያለው የተፋጠ ጠ ልዩነት የማይታያቸው፥ ህዝቡን በጅምላ የሚፈርጁና አንዱ ህዝብ በሌላው ህዝብ ላይ እንዲዘምት እየቀሰ ቀሱ ተስፋኣጣዎች አሉ። እነዚህ በቃል የአህአዴግ ጠላቶች የሚመስሉ ኣጉል ታጋዮች በተግባር ግን የአህአዴ ግ ረዳቶች በመሆናቸው በቀላሉ የሚታዩ እንቅፋቶች ኣይደሉም። ሌላው እንቅፋት የኤህአዴግ ተስፈኞች ናቸ ው። የተቀናጀላቸው ፕሮፓጋንዳ በመንዛት የትግሉን አቅጣጫ ያዛንፋሉ። በአሁኑ ወቅቱ የሚያካሂዱት ቅስቀሳ እንመልከት ፣ <u>የአህአዴግ</u> <u>አመራር በእውነቱ ብዙ ስሕተት ፈጽመዋል</u>። <u>ኣመራሩ እራሱ ተበላሽቶ ሃገሩንም ኣ በላሽቶታል</u>። ግን <u>አሁን እንተካው ቢባል ማን ይተካዋል ። ተቃዋሚው ብዛቱም ይሁን ክፍፍሉ አያድርስ ነ ው</u>። <u>የተቀናጀ ትግል ማካሄድ ኣልቻለም</u>። <u>ከዛም በላይ አህአዴግን ለማስወገድ ትግል ማካሄድ ህዝቡ አይደግ ፈውም፥ ትግል ሰልችቶታል</u>። ይሉታል። ባጭሩ ኤህአዴግ ካለበት ይቆይ፥ ኣትታገሉት የሚል የሆዳሞች ጸራ ምዝብሩ ህዝብ ቅስቀሳ ነው። እነዚህንና የመሳሰሉትን እንቅፋቶች በግልጽ መድረክ ማጋለጥና መዋጋት አስፈ ላጊ ይሆናል። እንደ ሌሎቹ ችግሮች ትኩረት የሚጠይቅ ኣንዱ የትግል ዘርፍ ነው።

በማጠቃለል የትግሉ ሂደት ብዙ ዘርፍ ያለው፥ ባንድ ወይም ሁለት ወቅታዊ እንቅስቃሴዎች የማይመለስ፥ ለ መሰረታዊ መፍትሄው ኤህአዴግን ማስወገድ ማእከል ኣድርጎ የሚቀናጅ ትግል መሆን ይኖርበታል። የኤህአዴግ መወገድ የትግሉ ማእከል ማድረግ ያስፈልጋል ስንል ኤህአዴግ ለሃገር ጥቅምና ለህዝብ መብት መከበር መ ቆም የማይችል፥ የእድገት ጸርና በሙስና የተዘፈቀ ኣጥፊ ቡድን በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ለእድገታችንና ለአንድ ነታችን ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በኣለም ኣቀፍ መድረክና ደንቦች ተከራክረን መብታች እንዳናስከብር ጭም ር በሩ ስለዘጋብን ነው።

የኤህአዴግ መወገድ የትግሉ ማእከል መሆን ያስፈልጋል ስንል የሁሉም ችግሮቻችን መሰረታዊው መፍትሄ ከዛ ው ውጤት ጋር በቀጥታ ስለሚያያዝ ነው። ኣምባገነኑ አህአዴግ ይወገድ ማለት ብቻ ደግሞ ኣይበቃም። ት ግሉ ኣምባገነን ስርኣት የሚወገድበትን ስትራተጂና ስልት መንደፍ፥ ለተነደፈው የትግል ኣቅጣጫ የሚበጅ ድ ርጅትና ኣመራር መስጠት፥ ከዚህም ኣልፎ ወዴት እንደሚያመራና ግቡ ምን እንደሚመስል ለሚመለከተው ሰ ፊው ህዝብ ጎልቶ እንዲታየውና ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ የምያስችል መሆን ኣለበት።

ይህ ይዋል ይደር የማይባልለት የኤትዮጵያችን ዘርፈ ብዙ ችግር ኣክትሞ፣ ህዝቡ ያለ ኣፈና በእኩልነት ይበ ለጽግ ዘንድ መከተል ያለብን የትግል ኣቅጣጫ በጥቅሉ ሲታይ ይኸው ይመስለናል። የትግርይ ዴሞክራሲያዊ ትብብር (ት ዴ ት) በዚህ የትግል ኣቅጣጫ ሲሰማራ በየኣከባቢው ተቀስቀሰው ያሉትን ተጨባጭ ትግሎች እ ንዲጠናከሩ እየተባበረ፥ ከዚህ በፊት የዘረጋውን የውህደት ጥሪ ምላሽ እንዲያገኝና ኣንድ ሃገር ኣቀፍ ዴሞክ ራሲያዊ ድርጅት ተፈጥሮ በውህደት እንድንዘምት እየተማጸነም ነው።

በተባበረው ክንዳችን ኣምባገነኖቹ ይወገዳሉ ፥ የኣትዮጵያ ብሩህ ተስፋ እውን ይሆናል ።

ት ዴ ት
የካቲት 2002